https://chilot.me

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፲፪
አዲስ አበባ የካቲት ፲፮ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

27th Year No.12
ADDIS ABABA 16th Feburary, 2021

ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፬፻፹፪/፪ሺ፲፫

የኢትዮጵያ የተቀማጭ ገንዘብ መድን ፈንድ ማቋቋሚያ እና አስተዳደር ደንብ .....ገጽ ፲፪ሺ፬፻፶፫

Content

Regulation No. 482/2021

Establishment and Operation of Ethiopian Deposit Insurance Fund Council of Ministers Regulation.....Page 12953

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፹፪/፪ሺ፲፫ የኢትዮጵያ የተቀማጭ ገንዘብ መድን ፈንድ ለማቋቋምና ለማስተዳደር የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

ለኢትዮጵያ ቀጣይ የኢኮኖሚ እድገት የሀገሪቱን የፋይናንስ ሥርዓት ጤናማ፣ ለአደጋ ያልተጋለጠና የተረጋጋ በማድረግ ማጠናከር አስፈላጊ በመሆኑ፤

የገንዘብ አስቀማጮች ጥበቃ ለፋይናንስ ሥርዓት መረጋጋት አስተዋጽኦ ያለው በመሆኑ፤

የተቀማጭ ገንዘብ መድን ፈንድ እንደ አንድ ተጨማሪ የሀገሪቱ የፋይናንስ ዘርፍ ማረጋጊያ ማቋቋም አስፈላጊ በመሆኑ፤

በመድን ክስተት ወቅት በመድን የተሸፈነ ተቀማጭ ገንዘብ ላለዉ አባል የፋይናንስ ተቋም ገንዘብ አስቀማጮች ክፍያ መፈጸም የሚያስችል ፈንድ ማቋቋምና ማስተዳደር አስፈላጊ በመሆኑ፤

ከብሔራዊ ባንክ፣ ከአባል ፋይናንስ ተቋማትና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር በመሥራት ተጋላጭነትን መቀነስና ለፋይናንስ ሥርዓቱ መረጋጋት አስተዋጽኦ ማድረግ ተገቢ በመሆኑ፤

COUNCIL OF MINISTERS REGULATION NO.482/2021
ESTABLISHMENT AND OPERATION OF ETHIOPIAN DEPOSIT INSURANCE FUND COUNCIL OF MINISTERS REGULATION

WHEREAS, for the ongoing economic development of Ethiopia it is essential to strengthen the country´s financial system by ensuring its safety, soundness and stability;

WHEREAS, the protection of depositors contributes to the stability of the financial system;

WHEREAS, it is essential to introduce deposit insurance fund as an additional element of the country´s financial safety net;

WHEREAS, it is necessary to establish and operate a Fund to enable payment to the member financial institution's depositors with insured deposits in case of the insurance event;

WHEREAS, it is vitally important to collaborate with the National Bank, Member Financial Institutions and other stakeholders to mitigate risk and contribute to stability of the financial system;

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹፻፩
Negarit G. P.O.Box 80001

https://chilot.me

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፭፻፺፩/፪ሺ (እንደተሻሻለ) አንቀጽ /፸፭/ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌዎች

፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ የተቀማጭ ገንዘብ መድን ፈንድ ማቋቋሚያ እና አስተዳደር ደንብ ቁጥር ፩፻፹፪/፪ሺ፲፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፣ በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩/ "ቦርድ" ማለት የፈንዱ የዳይሬክተሮች ቦርድ ነው፤

፪/ "የፋይናንስ ተቋም ዋና ሥራ አስፈጻሚ" ማለት በማናቸውም የማዕረግ ስም የሚጠራ ቢሆንም የአንድን ፋይናንስ ተቋም የዕለት ተዕለት ሥራዎች በዋና ኃላፊነት የመምራት ሥልጣን የተሰጠው ሰው ነው፤

፫/ "የፈንዱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ" ማለት በዚህ ደንብ አንቀጽ /፲፫/ መሠረት የተሾመ የፈንዱ ኃላፊ ነው፤

፬/ "ዳይሬክተር" ማለት በማናቸውም የማዕረግ ስም የሚጠራ ቢሆንም የአንድ ፋይናንስ ተቋም የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ነው፤

፭/ "የፈንዱ ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚ" ማለት የፈንዱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ምክትል የሆነና በዚህ ደንብ አንቀጽ /፲፫/ መሠረት የፈንዱ ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚ ተደርጎ የተሾመ ኃላፊ ነው፤

፮ / "ተቀማጭ ገንዘብ" ማለት በቁጠባ፣ በተንቀሳቃሽ፣ በጊዜ ገደብ እና በሌሎች መሰል ተቀማጭ ሂሳቦች ውስጥ የሚገኝ የገንዘብ አስቀማጩ ያልተከፈለ ጠቅላላ ገንዘብ ነው፤

NOW, THEREFORE, pursuant to Article 25 of the National Bank of Ethiopia Establishment Proclamation No. 591/2008 (as Amended), the Council of Ministers has issued this Regulation.

PART ONE

GENERAL PROVISIONS

1. Short Title

This Regulation may be cited as the "Establishment and Operation of Ethiopian Deposit Insurance Fund Council of Ministers Regulation No.482/2021".

2. Definitions

In this Regulation, unless the context requires otherwise:

1/ "Board" means the board of directors of the Fund;

2/ "Chief executive officer of a financial institution" means a person, by whatever title that person may be referred to, who is primarily responsible for the day-to-day management of the affairs of a financial institution;

3/ "Chief executive officer of the Fund" means the Head of the Fund appointed as per Article 13 of this Regulation**;**

4/ "Director" means any member of the board of directors of a financial institution by whatever title he may be referred to**;**

5/ "Deputy chief executive officer of the Fund" means any officer of the Fund who is Deputy to the Chief Executive Officer of the Fund and appointed as per Article 13 of this Regulation;

6/"Deposit money" means aggregate of the unpaid balance due to a depositor in respect of all his accounts,saving, circulating and other related by whatever name it may be called;

https://chilot.me

፯/ **"የገንዘብ አስቀማጭ"** ማለት የፈንዱ አባል በሆነ የፋይናንስ ተቋም ውስጥ በተቀማጭ መልክ ገንዘብ ያለው ሰው ነው፤

7/**"Depositor of money "** means a person who holds funds as a deposit with a member financial institution;

፰/ **"ሠራተኛ"** ማለት የሥራ አስፈጻሚ አመራር አባላትን ጨምሮ ከፈንዱ ጋር ቋሚ የቅጥር ውል የፈፀመ ሰው ነው፤

8/**"Employee"** means a person who has entered into a permanent employment agreement with the Fund and includes members of executive management;

፱/ **"የሥራ አስፈጻሚ አመራር"** ማለት የፈንዱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ እና/ወይም ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚ ናቸው፤

9/**"Executive Management"** means the Chief Executive Officer and/or the Deputy Chief Executive Officer of the Fund;

፲/ **"የወደቀ የፋይናንስ ተቋም"** ማለት በባንክ ሥራ አዋጅ ቁጥር ፭፻፺፩/፪ሺ (እንደተሻሻለ) አንቀጽ /፴፪/ እና /፵/፪/ እንዲሁም በአነስተኛ የፋይናንስ ሥራ አዋጅ ቁጥር ፭፻፳፭/፪ሺ፩ (እንደተሻሻለ) አንቀጽ /፰/ መሠረት ብሔራዊ ባንክ የሥራ ፈቃዱ መሰረዙን ያሳወቀው አባል የፋይናንስ ተቋም ነው፤

10/ **"Failed Financial Institution"** means a member financial institution that has been notified the revocation of the business license by the National Bank as per Article 32 and 40(2) of Banking Business Proclamation No. 592/2008 as amended by Banking (Amendment) Proclamation No. 1159/2019 and Article 8 of Micro-Financing Business Proclamation No. 626/2009 as amended by Microfinance Business (Amendment) Proclamation No. 1164/2019;

፲፩/ **"የፋይናንስ ተቋም"** ማለት በብሔራዊ ባንክ ፈቃድ የተሰጠዉ ማንኛዉም የንግድ ባንክ ወይም አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ማለት ነዉ፤

11/ **"Financial Institution"** means a commercial bank or a microfinance institution licensed by the National Bank;

፲፪/ **"መንግሥት"** ማለት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ነዉ፤

12/ **"Government"** means the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;

፲፫/ **"ገዥ፣ ምክትልገዥ፣ የባንኪንግ ቁጥጥር ዳይሬክተር፣ የአነስተኛ ፋይናንስ ተቋማት ቁጥጥር ዳይሬክተር"** ማለት እንደ ቅደም ተከተላቸዉ የብሔራዊ ባንክ ገዥ፣የፋይናንስ ተቋማት ቁጥጥር ምክትልገዥ፣ የባንኪንግ ቁጥጥር ዳይሬክተር እና የአነስተኛ ፋይናንስ ተቋማት ቁጥጥር ዳይሬክተር ማለት ነዉ፤

13/ **"Governor, Vice Governor, Banking Supervision Director, Microfinance Institutions Supervision Director"** means Governor, Financial Institutions Supervision Vice Governor, Banking Supervision Director and Microfinance Institutions Supervision Director of the National Bank;

፲፬/ **"ተደማጭነት ያለው ባለአክሲዮን"** ማለት በሚመለከተዉ የፋይናንስ ተቋም በብሔራዊ ባንክ መመሪያ እንደተገለጸዉ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በማናቸውም የፈንዱ አባል በሆነ የፋይናንስ ተቋም ውስጥ ተደማጭ የሚያደርገዉ የአክሲዮን ድርሻ ያለው ሰው ነው፤

14/ **"Influential shareholder"** means a person who holds directly or indirectly a certain percent or more of the total subscribed capital of a member financial institution as defined in the National Bank Directive of respective financial institution;

https://chilot.me

፲፭/ "መነሻ ዓረቦን" ማለት በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፮/፩ እና ፳፬/፫ መሠረት ለፈንዱ መነሻ ካፒታል እንዲሆን በፈንዱ አባል የፋይናንስ ተቋም የሚከፈል የተወሰነ የገንዘብ መጠን ነው፤

15/ **"Initial premium"** means a fixed amount payable by a member financial institution for the establishment of the Fund as initial capital as provided in Articles 16(1) & 24(3) of this Regulation;

፲፮./ "በመድን የተሸፈነ ተቀማጭ ገንዘብ" ማለት በዚህ ደንብ ድንጋጌዎች መሠረት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ፈንዱ የመድን ሽፋን የሰጠዉ የአባል ፋይናንስ ተቋም ተቀማጭ ገንዘብ ነው፤

16./ **"Insured Deposit money"** means the deposit or any portion thereof of a member financial institution the repayment of which is insured by the Fund under the provisions of this Regulation;

፲፯/ "የመድን ክስተት" ማለት በመድን የተሸፈነዉን ተቀማጭ ገንዘብ ክፍያ ፈንዱ እንዲፈፅም ተገቢ የሚሆንበት ክስተት ነዉ፤

17/ **"Insurance Event"** means an event that requires the Fund to undertake payment of insured deposits money;

፲፰/ "የጋራ ተቀማጭ ገንዘብ" ማለት በሁለት ወይም ከዚያ በላይ ሰዎች የተቀመጠ ገንዘብ ሆኖ የክፍያ ጥያቄ በሁሉም የሂሳቡ ባለቤቶች መቅረብ ያለበት ተቀማጭ ገንዘብ ነዉ፤

18/ **"Joint Deposit money "** means the deposit made by two or more persons, and the payment of which may be demanded by all the holders of that account;

፲፱/ "አባል የፋይናንስ ተቋም" ማለት ከሕዝብ ተቀማጭ ገንዘብ የሚሰበስብ እና በዚህ ደንብ ድንጋጌዎች መሠረት ለፈንዱ ዓረቦን መክፈል የሚጠበቅበት የፋይናንስ ተቋም ነው፤

19/ **"Member Financial Institution"** means a member financial institution that accepts deposits from the general public; and required to pay premium to the Fund under the provisions of this Regulation;

፳/ "አባልነት" ማለት በዚህ ደንብ ድንጋጌዎች መሠረት የፈንዱ አባል መሆን ማለት ነው፤

20/ **"Membership"** means being a member of the Fund in line with provisions of this Regulation;

፳፩/ "ብሔራዊ ባንክ" ማለት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ነው፤

21/ "**National Bank**" means the National Bank of Ethiopia;

፳፪/ "ዓመታዊ ዓረቦን" ማለት በዚህ ደንብ አንቀጽ/፲፮ (፭) መሠረት በአባል የፋይናንስ ተቋም ለፈንዱ የሚከፈል ገንዘብ ነው፤

22/ **"Annual Premium"** means the sum payable by a member financial institution to the Fund as provided in Article 16 (5) of this Regulation;

፳፫/ "ከወደቀ የፋይናንስ ተቋም ያተረፈ ሰው" ማለት ከወደቀው የፋይናንስ ተቋም ጉዳት ያልተገባ ጥቅም ወይም ትርፍ ያገኘ የገንዘብ አስቀማጭ ነው፤

23/ **"Profited from the failed financial institution"** means a depositor who obtained any benefit or gain at the expense of the failed financial institution

፳፬/ "የፋይናንስ ተቋም ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚ" ማለት የማንኛዉም ፋይናንስ ተቋም ዋና ሥራ አስፈጻሚ ምክትል የሆነ ወይም ተጠሪነቱ በቀጥታ ለፋይናንስ ተቋሙ የዳይሬክተሮች ቦርድ የሆነ ማንኛውም የሥራ ኃላፊ ነው፤

24/ **"Senior Executive officer of a financial Institution"** means any officer of a financ ial institution who is deputy to the chief executive officer of a financial institution or is directly accountable to the board of directors of a financial institution;

https://chilot.me

ሸ/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

ቀ/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸዉ ሴትንም ይጨምራል፡፡

፫. **የተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ ደንብ በፋይናንስ ተቋማት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

ክፍል ሁለት

ስለፈንዱ መቋቋም፣ ሥልጣንና ተግባር እና አደረጃጀት

፬. **መቋቋም**

፩/ የኢትዮጵያ የተቀማጭ ገንዘብ መድን ፈንድ (ከዚህ በኋላ "ፈንድ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ ሕጋዊ ሰዉነት ያለዉ ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፣

፪/ የፈንዱ ተጠሪነት ለብሔራዊ ባንክ ይሆናል፡፡

፭. **ዋና መሥሪያ ቤት**

የፈንዱ ዋና መ/ቤት በአዲስ አበባ ከተማ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በክልሎች ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ሊኖሩት ይችላል፡፡

፮. **የፈንዱ ሥልጣንና ተግባራት**

ፈንዱ ዓላማዉን ለማሳካት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ መነሻና ዓመታዊ የአረቦኖች መጠን መወሰን፣

፪ /በመድን ለተሸፈነ ተቀማጭ ገንዘብ የሽፋን ጣሪያ መወሰን፣ አስፈላጊ ሲሆን ማሻሻል፣

፫/ ለፈንዱ የሚቀርቡ የካሣ ክፍያ ጥያቄዎችን መገምገም፣

፬/ የገንዘብ እጥረት ሲያጋጥመዉ፣ ከመንግሥት እና/ወይም ከሌሎች ምንጮች ብድር የሚያገኝ በትን ፖሊሲ ማዉጣት፣

25/ "**Person**" means any natural or juridical person;

26/ Any expression in the masculine gender includes the feminine.

3. **Scope of Application**

This Regulation shall be applicable to all financial institutions.

PART TWO
ESTABLISHMENT, POWER, AND FUNCTIONS, AND ORGANIZATION OF THE FUND

4. **Establishment of the Fund**

1/ Ethiopian Deposit Insurance Fund (here after shall be referred to as "the Fund") having its own juridical personality is established by this Regulation.

2/ The Fund shall be accountable to the National Bank.

5. **Head Office of the Fund**

The Fund shall have its Head Office in Addis Ababa and may establish branches in Regional states.

6. **Power and Functions of the Fund**

For the fulfillment of its objectives, the Fund shall have the following powers and duties:

1/ determine initial and annual premiums;

2/ set and regularly revise the coverage limits for insured money deposits;

3/ assess compensation claims made against the Fund;

4/ set borrowing policy to find from Government and/or other sources if there is shortage of funds;

https://chilot.me

፭/ ለግንዘብ አስቀማጮች የፈጸማቸዉን ክፍያዎች ከወደቁ የፋይናንስ ተቋማት የንብረት ማጣራት ተመላሽ ማድረግ፣

5/ recover the payments made from liquidation proceeds of failed financial institutions;

፮/ የፈንዱን ሀብት ኢንቨስት ማድረግና ማስተዳደር፣

6/ invest and manage resources of the Fund;

፯/ ከዓለም አቀፍ የተቀማጭ ገንዘብ መድን ሰጪ አካላት ጋር መተባበር፣

7/ collaborate with international money deposit insurance bodies;

፰/ የዓረቦን ክፍያዎችን ከአባል የፋይናንስ ተቋማት እንዲሁም የተለያዩ መዋጮዎችን እንደ መንግሥትና የልማት አጋሮች ካሉ ሌሎች ምንጮች መሰብሰብና ወደ ፈንዱ ሂሳብ ገቢ ማድረግ፣

8/ collect premiums from member financial institutions and various contributions from other sources like government and development partners and deposit in the account of the Fund;

፱/ በመድን የተሸፈነዉን ተቀማጭ ገንዘብ አስፈላጊዉን መስፈርት ላሟሉ አስቀማጮች መክፈል፣

9/ make payments to eligible depositors to the extent of insured deposits;

፲/ ስለ ተቀማጭ ገንዘብ መድን ሥርዓቱ የሕዝቡን ግንዛቤ ማሳደግ፣

10/ raise public awareness about the system of insured deposit money ;

፲፩/ ከአባል የፋይናንስ ተቋማት መረጃዎችን መሰብሰብና ወቅታዊ ሪፖርቶችን ማዘጋጀት፣

11/ collect information from member financial institutions and reports prepare periodic;

፲፪/ ለአባል የፋይናንስ ተቋም መውደቅ ምክንያት እንደሆኑ የተጠረጠሩ አካላትን ለሕግ ማቅረብና የፍርድ ሂደቱን መከታተል፣

12/ deal with parties at fault in a member financial institution’s failure and manage court cases;

፲፫/ ከብሔራዊ ባንክ ጋር በቅንጅትና በቅርበት መሥራት፣

13/ work and collaborate closely with the National Bank;

፲፬/ ውል መዋዋል፣

14/ Make contract;

፲፭/ መክሰስና መከሰስ፣

15/ sue and be sued;

፲፮/ ንብረት መያዝ፣ ማግኘት፣የንብረት ባለቤት መሆን እና ንብረቱን በሽያጭ ወይም በሌላ መንገድ ማስወገድ፣ እና

16/ acquire, own, possess and dispose its property by sale or in any other manner; and

፲፯/ ከዓላማዉ ጋር የማይቃረኑ እስከሆነ ድረስ ለፈንዱ የሥራ ቅልጥፍና አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተግባራትን ማከናወን፡፡

17/ Conduct any other activities necessary for the efficient function of the Fund provided that they do not contradict its objectives.

https://chilot.me

፯. **<u>የፈንዱ አደረጃጀት</u>**

ፈንዱ፡

፩/ የዳይሬክተሮች ቦርድ (ከዚህ በኋላ "ቦርድ" እየተባለ የሚጠራ)፣

፪/ ዋና ሥራ አስፈጻሚና ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚ፣ እና

፫/ አስፈላጊ ሠራተኞች ይኖሩታል።

፰. **<u>የፈንዱ ቦርድ አባላት</u>**

የፈንዱ ቦርድ ሰባት አባላት ይኖሩታል። ገዥ፣ የገንዘብ ሚኒስትር፣ ምክትል ገዥ፣ የባንኪንግ ቁጥጥር ዳይሬክተር እና የአነስተኛ ፋይናንስ ተቋማት ቁጥጥር ዳይሬክተር የቦርዱ ቋሚ አባላት ይሆናሉ። በዘርፉ በቂ ዕዉቀት ያላቸዉ ቀሪዎቹ ሁለት አባላት በባንኮችና በአነስተኛ ፋይናንስ ተቋማት ማኅበራት አቅራቢነት በመንግሥት ይሾማሉ።ቦርዱ ከሠራተኛዉ የሚወከል የራሱ ፀሐፊ ይኖረዋል።

፱. **<u>የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር</u>**

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ ይህን ደንብ ፈንዱ በአግባቡ መተግበሩን ማረጋገጥ፣

፪/ በተቀማጭ ገንዘብ መድን አሰጣጥ ዙሪያ ሊደረግ ስለሚገባዉ የሕግ፣ የቁጥጥርና የፖሊሲ ማሻሻያ መንግሥትን ማማከር፣

፫/ የፈንዱን ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ የጥቅም ግጭት መቆጣጠሪያና የሥነምግባር መመሪያዎች እና መዋቅር ማጽደቅ፣

፬/ የፈንዱን የፋይናንስና ኦፕሬሽን ዕቅዶች፣ በጀትና የሂሳብ መግለጫዎች ማጽደቅ፣

፭/ ለዚህ ደንብ ተፈጻሚነት አስፈላጊ የሆኑ የቁጥጥር መመሪያዎችን ማውጣት፣

፮/ እንደ አስፈላጊነቱ ለዚህ ደንብ ማሻሻያ የሚሆኑ ሀሳቦችን ለመንግሥት ማቅረብ፣

7. <u>Organization of the Fund</u>

The Fund shall have:

1/ Board of Directors (here after will be referred to as "Board";

2/ Chief Executive Officer and Deputy Chief Executive Officer; and

3/ Necessary staff.

8. <u>Board Members of the Fund</u>

The Board of the Fund shall be composed of seven members. Governor, Minister of Finance, Vice Governor, Banking Supervisio n Director and the Microfinance Institutions Supervision Director shall be permanent ex-officio members of the Board. The remaining two members of the Board with knowledge in the area shall be appointed by the Governmen t based on recommendations from bankers and microfinance institutions associations. The Board shall have its own secretary designated from staff of the Fund.

9. <u>Powers and Duties of the Board</u>

The Board shall have Powers and Duties to:

1/ ensure the proper implementation of this Regulation by the Fund;

2/ advise the Government on legislative, regulatory and policy reforms with regard to deposit money insurance;

3/ approve policies, strategies, conflict of interest rules and codes of coducts, and structure of the Fund;

4/ approve the financial and operational plans, budget and financial statements of the Fund;

5/ issue regulatory directives necessary for the implementation of this Regulation;

6/ propose ideas of amendments to this Regulation for the Government when necessary;

https://chilot.me

፯/ በመድን ክስተት ወቅት ለገንዘብ አስቀማጮች የሚፈጸሙትን ክፍያዎች ማጽደቅ፣

7/ approve payments to money depositors in case of an insurance event;

፰/ ለአስቸኳይ ጉዳይ የሚሆን የገንዘብ ምንጭና ብድር ማጽደቅ፣

8/ approve source funding and borrowing for emergency purposes;

፱/ በፈንዱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በሚቀርብ ምክረ ሀሳብ መሠረት በቦርዱ እምነት ለፈንዱ ሥራ የሚያስፈልገዉን ሠራተኛ ብዛት መወሰን፣

9/ determine the number of staff with in the opinion of the Board which required for carrying out the functions of the Fund as recommended by the Chief Executive Officer of the Fund;

፲/ ፈንዱ አባል የሚሆንባቸውን ዓለም አቀፍ አካላት መወሰን፣

10/ approve international bodies in which the Fund may become a member;

፲፩/ የፈንዱን የውጪ ኦዲተር መሾም፣

11/ appoint external Auditor for the Fund;

፲፪/ የፈንዱን የሥራ አፈፃፀም መከታተልና መገምገም፣

12/ monitor and evaluate activities of the Fund;

፲፫/ በቦርዱ እምነት የፈንዱን ሥልጣንና ተግባር በበቂ ሁኔታ ለመፈፀም የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ፣ ተጨማሪ እና አስቻይ ተግባራትንና ግብይቶችን መፈጸም፣ እና

13/ perform such other activities and enter into such other transactions which in the opinion of the Board are reasonabl y incidental, supplementary or conduct ive to the exercise of the power and performance of the Fund; and

፲፬/ ቦርዱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘዉ ሥልጣኑን ለፈንዱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በዉክልና ማስተላለፍ።

14/ The Board may, where it deems necessary, delegate its powers to the Chief Executive Officer of the Fund.

፲. ስለቦርዱ አባላት ክፍያ

ለቦርድ አባላት የሚከፈለው አበል መጠን በመንግሥት ይወሰናል።

10. Remuneration of the Board

The Government shall fix the amount of allowance payable to the members of the Boar

፲፩. የቦርድ ስብሰባ

፩/ ከቦርድ አባላት አራቱ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል። ሆኖም ከተገኙት አባላት ውስጥ አንዱ ገዥ ወይም ምክትል ገዥ መሆን አለበት።

11. Board Meeting

1/ The presence of four members of the Board shall constitute a quorum; provided, however, that one of them shall be the Governor or the Vice Governor.

፪/ የቦርዱ ስብሰባ በሰብሳቢዉ ወይም እርሱ ባልተገኘ ጊዜ በምክትል ሰብሳቢዉ ወይም ሁለቱም ባልተገኙ ጊዜ ሰብሳቢዉ በወከለው የቦርድ አባል ይጠራል።

2/ Meeting of the Board shall be called by the Chairperson or, in his absence, by Deputy Chairperson, or in absence of both by a Board member assigned by the Chairperson

https://chilot.me

፫/ የቦርድ ሰብሳቢዉ በሚኖርበት ጊዜ የቦርዱን ስብሰባዎች ይመራል፡፡ እርሱ ባልተገኘ ጊዜ ምክትል ሰብሳቢዉ ስብሰባዎችን ይመራል ወ ይም ሁለቱም ባልተገኙ ጊዜ ሰብሳቢዉ በወክ ለዉ የቦርድ አባል ስብሰባው ይመራል፡፡

3/ The Chairperson shall, whenever present, preside over meetings of the board. In the absence of the Chairperson, Deputy Chairperson shall preside over such meetings or in absence of both Chairpersons a board member of the Fund, who is designated for this purpose by the Chairperson, shall preside over such meeting.

፬/ የቦርድ ስብሰባ ቢያንስ በሦስት ወር አንድ ጊዜ ይካሄዳል፡፡ ሆኖም ሰብሳቢዉ ወይም እርሱ ባልተገኘ ጊዜ በእርሱ የተወከለ ሰው ወይም የፈንዱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይም ከቦርዱ አባላት ሦስቱ ሲጠይቁ ስብሰባው በማናቸውም ጊዜ ሊጠራ ይችላል፡፡

4/ Meeting of the Board shall be held at least once every three months; provided, however, that the Chairperson or, in his absence the person delegated by him, may call a meeting at any time or when the Chief Executive Officer of the Fund or three board members so request.

፭/ ማንኛዉም የቦርድ ውሳኔ በስብሰባው በተገኙት አባላት አብላጫ ድምጽ ይወሰናል፡፡ ቦርዱ በድምጽ እኩል ለእኩል በተከፈለ ጊዜ ሰብሳቢዉ ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡

5 / All decisions of the Board shall be made by a simple majority vote of the members present. In case of a tie, the Chairperson shall have a casting vote.

፮/ የቦርድ ስብሰባዎች ቃለ ጉባኤዎች በትክክልና ቦርዱ በሚወስነው አኳኋን ይመዘገባሉ፡፡ በቦርዱ ካልተፈቀደ በቀር ቃለ ጉባኤዎች በምስጢር ይጠበቃሉ፡፡

6/ Minutes of meetings of the Board shall be recorded accurately and in such form as the Board may determine. Unless the Board decides otherwise, minutes of the Board shall be confidential

፯/ ከፈንዱ ሥራ ጋር የሚጋጩ የግል ጥቅሞች ያሉት የትኛዉም የቦርድ አባል ይህንኑ በጽሑፍ ለቦርዱ ማሳወቅ አለበት፣ በእነዚህ ጉዳዮች ዙሪያ በሚደረጉት የቦርድ ውይይ ቶችም አይሳተፍም፡፡

7/ A Board member shall disclose to the Board in writing any personal interests in the activities of the Fund and shall not be present in the deliberations of the Board in respect of that matter.

፲፪. <u>የቦርድ አሠራር</u>

12. <u>The Board Procedure</u>

፩/ ቦርዱ የራሱን የአሠራር መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

1/ The Board may adopt its own rules of procedure.

፪/ ቦርዱ ውሳኔዎቹን ለማቀላጠፍ ኮሚቴ ሊያቋቁም ይችላል፡፡

2/ The Board may establish a committee to facilitate its decisions.

፲፫. <u>የፈንዱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ እና ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሹመት</u>

13. <u>Appointment of Chief Executive Officer and Deputy Chief Executive Officer of the Fund</u>

፩/ የፈንዱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ እና ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚ በብሔራዊ ባንክ አቅራቢነት በመንግሥት ይሾማሉ፡፡

1/ A Chief Executive Officer and Deputy Chief Executive Officer of the Fund shall be appointed by the Government as recommended by the National Bank.

https://chilot.me

፪/ የፈንዱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ የፈንዱ ዋና ተጠሪ ይሆናል።

2/ The Chief Executive Officer of the Fund shall be the principal representative of the Fund.

፫/ የፈንዱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ እና ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚ ፈንዱን ከለቀቁ በኋላ ባለዉ አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በየትኛዉም የፋይናንስ ተቋም ውስጥ አማካሪ ወይም ሠራተኛ ሆነው መሥራት አይችሉም፡፡

3/ The Chief Executive Officer and the Deputy Chief Executive Officer of the Fund shall not work for any financial institution, neither as consultant nor as employee, within a period of one year after the termination of their assignment for the Fund.

፲፬. የፈንዱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሥልጣንና ተግባር

የፈንዱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡-

፩/ በዚህ ደንብና በቦርዱ ውሳኔዎች መሠረት የፈንዱን ሥራ ይመራል፣ ይቆጣጠራል፣

፪/ የፈንዱን ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ የአሠራር መመሪያዎች፣ ዕቅዶች እና ዓመታዊ በጀቶች ያዘጋጃል፣ በቦርድ ሲጸድቁ በሥራ ላይ ያውላል፣

፫/ የቁጥጥር መመሪያዎችን አዘጋጅቶ ለቦርድ ውሳኔ ያቀርባል፣

፬/ የሲስተም፣ የመዋቅር እና የሰው ኃይል ፍላጎት ምክረ ሀሳብ ለቦርዱ ያቀርባል፣ በቦርድ ሲጸድቅም በሥራ ላይ ያውላል፣

፭/ ፈንዱን በተለያዩ መድረኮች ይወክላል፣

፮/ ፈንዱን የሚመለከቱ ውሎችን፣ ደብዳቤዎችን እና ሌሎች ሰነዶችን ይፈርማል፣

፯/ ለፈንዱ ውጤታማነትና የሥራ ቅልጥፍና አስፈላጊ በሆነ መጠን፣ ሥልጣኑንና ተግባሩን ለፈንዱ ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚና ለሠራተኞች በከፊል በዉክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፣

፰/ በፈንዱ የወደፊት ስትራቴጂካዊ አቅጣጫ ላይ የጎላ ጉዳት ሊያስከትል ስለሚችል ማንኛዉም ጉዳይ ለቦርዱ ያሳዉቃል፣

፱ /ሌሎች ተዛማጅ ሥራዎችን ያከናዉናል፡፡

14. Powers and Duties of the Chief Executive Officer of the Fund

The Chief Executive Officer of the Fund shall:

1/ direct and supervise operations of the Fund in accordance with this Regulation and the decisions of the Board;

2/ prepare policies, strategies, procedures, plans and annual budgets of the fund, and upon approval by the Board implement the same;

3/ propose regulatory directives and submit to the Board decesion;

4/ propose system, structure and human resource requirement to the Board, and upon approval by the Board implement the same;

5/ represent the Fund on different stages ;

6/ sign contracts, correspondences and other documents for the Fund;

7/ delegate part of his Powers and Duties to the Deputy Chief Executive Officer and employees of the Fund to the extent necessary for the effectiveness and efficiency of the Fund;

8/ keep the Board informed of any matter that could materially affect the strategic direction of the Fund; and

9/ Carry out other related activities.

https://chilot.me

፲፭. የፈንዱ ምክትል ዋና ሥራ አስፈፃሚ ሥልጣንና ተግባር

የፈንዱ ምክትል ዋና ሥራ አስፈፃሚ የፈንዱን ዋና ሥራ አስፈፃሚ ይረዳል፤ የፈንዱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ በሌለ ጊዜ ለፈንዱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ የተሰጡትን ሥራዎች በሙሉ ያከናውናል::

15. Powers and Duties of the Deputy Chief Executive Officer of the Fund

The Deputy Chief Executive Officer of the Fund shall assist the Chief Executive Officer of the Fund and in the absence of the Chief Executive Officer of the Fund shall discharge all the functions conferred on the Chief Executive Officer of the Fund.

ክፍል ሶስት

ፋይናንስ ነክ ድንጋጌዎች

PART THREE

FINANCIAL PROVISONS

፲፮. ስለአረቦን ክፍያ

፩/ ሁሉም አባል የፋይናንስ ተቋማት ይህ ደንብ ሥራ ላይ በዋለ በ፴ ቀናት ውስጥ ከፈንዱ ጋር የአባልነት ውል ተፈራርመው በፈንዱ የሚወሰነዉን መነሻ የዓረቦን ክፍያ ወደ ፈንዱ ሂሳብ ገቢ ያደርጋሉ፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት የሚደረገው መነሻ የዓረቦን ክፍያ የፈንዱ መነሻ ካፒታል ይሆናል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ ላይ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ መነሻ የዓረቦን ክፍያ ባይፈጸም ፈንዱ በቀሪው የገንዘብ መጠን ላይ ክፍያው ለዘገየበት ጊዜ የቅጣት ምጣኔ ይጥላል፡፡ የቅጣት ምጣኔዉ በፈንዱ ይወሰናል፡፡

፬/ ተጨማሪ መነሻ ካፒታል እንዲሆን መንግሥት ብር ፪፻ ሚሊዮን (ሁለት መቶ ሚሊዮን ብር) ለፈንዱ ይመድባል፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የአባልነት ውል የፈረሙ ሁሉም አባል የፋይናንስ ተቋማት የአማካይ ተቀማጭ ገንዘባቸዉን 0.3 በመቶ ዓመታዊ የዓረቦን ክፍያ ለፈንዱ ይፈጽማሉ፡፡

፮/ ጤናማ ያልሆነ የፋይናንስ ተቋም ስለሚፈፅመዉ የተለየ መነሻ የዓረቦን ክፍያ ፈንዱ በመመሪያ ሊወስን ይችላል፡፡

16. Payment of Premium

1/ All member financial institutions, within 30 days from the effective date of this Regulation, shall sign membership contract with the Fund and pay to the Fund´s account an initial premium to be determined by the Fund.

2/ The initial premium contributed in line with Sub-Article (1) of this Article shall be considered as initial capital of the Fund.

3/ In case that the initial premium is not paid within the time specified in Sub-Article(1) of this Article, the Fund shall charge default interest rate on the due amount for the period of delay. The default interest rate shall be determined by the Fund.

4/ The Government shall contribute Birr 200 Million (Two Hundred Million Birr) to the initial capital of the Fund.

5/ All member financial institutions that signed membership contract as per Sub-Article (1) of this Article shall pay to the Fund annual premiums of 0.3% of their average deposits.

6/ The Fund may determine by a directive a special initial premium to be paid by a financial institution with poor financial soundness.

https://chilot.me

፯/ ፈንዱ በዓመታዊ የዓረቦን ክፍያ ላይ ማሻሻያ ከማድረጉ ከ፴ (ሰላሳ) ተከታታይ ቀናት አስቀድሞ ለአባል የፋይናንስ ተቋማት ማሳወቅ አለበት፡፡

፰/ ፈንዱ ከወደቁ ወይም ከፈረሱ የፋይናንስ ተቋማት የንብረት ማጣራት ከሚገኝ ተመላሽ ገንዘብና በቦርዱ ከሚጸድቁ ሌሎች የፋይናንስ ምንጮች ከሚገኝ ገንዘብ ተጠቃሚ ይሆናል፡፡

፲፯. የፈንዱ ሌሎች የገቢ ምንጮች

፩/ የፈንዱ ገንዘብ በብሔራዊ ባንክ በሚከፈት ሂሳብ ዉስጥ ይቀመጣል፡፡

፪/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮(፮) በተደነገገው መሠረት ፈንዱ ከተለያዩ የኢንቨስትመንት ሥራዎች ገቢ ሊያመነጭ ይችላል፡፡

፫/ በባንክ ሥራ አዋጅ ቁጥር ፭፻፺፪/፪ሺ (እንደተሻሻለ) አንቀጽ ፶፪/፩/ መሠረት የይገባኛል ጥያቄ ያልቀረበባቸዉንና ወደ ብሔራዊ ባንክ የተላለፉ የፋይናንስ ተቋም ተከፋይ ሂሳቦችን ፈንዱ ከብሔራዊ ባንክ በብድር ወስዶ ሊጠቀምባቸዉ ይችላል፡፡

፲፰. የገንዘብ አከል ሀብት እጥረት ሲያጋጥመዉ ፈንዱ ያሉት የፋይናንስ አማራጮች

፩/ በዚህ ደንብ መሠረት ፈንዱ የገንዘብ አከል ሀብት እጥረት ካጋጠመዉ ጉድለቱ ከሚከተሉት አማራጮች በአንዱ ወይም በጣምራ ይሸፈናል፡-

ሀ) ፋይናንስ ሥርዓቱ ላይ አጠቃላይ ቀዉስ የሚያስከትል ከሆነ ከመንግሥት በሚገኝ የገንዘብ ድጋፍ፣

ለ) በመድን በተሸፈነዉ ተቀማጭ ገንዘባቸዉ ድርሻ መጠን በአባል የፋይናንስ ተቋማት መዋጮ፣

ሐ) በአባል የፋይናንስ ተቋማት ዓመታዊ የዓረቦን ቅድሚያ ክፍያ፣እና

መ) ፈንዱ በሚያወጣቸው መስፈርቶች መሠረት በተለያዩ ብድሮች፡፡

7/ The Fund shall inform the member financial institutions at least 30 (thirty) calendar days before it revises the annual premium.

8/ The Fund shall use recoveries from assets of failed financial institutions in case of sale or liquidation, and other sources approved by the Board.

17. Other Incomes of the Fund

1/ The Fund´s resources shall be maintained in an account to be opened in the National Bank.

2/ The Fund may generate income from investment activities as stipulated under Article 6(6) of this Regulation.

3/ The Fund may use, by borrowing from the National Bank, unclaimed liabilities of a financial institution transferred to the National Bank in line with Article 52 (1) of the Banking Business Proclamation No. 592/2008 (as amended).

18. Financing the Fund when There is Shortfall of Resources

1/ If at any time, resources of the Fund fall short of its liabilities under this Regulation, such shortfall may be covered in any one or combination of :

a) bailout funding by the Government when the shortfall induces systemic crisis in the financial system;

b) requiring the member financial institutions to cover the shortfall in proportion to their insurable deposits;

c) requiring member financial institutions to pay advance annual premiums; and

d) drawing loans in accordance with the terms and conditions prescribed by the Fund.

https://chilot.me

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ሐ) መሠረት በቅድሚያ የተፈጸመ ዓመታዊ የዓረቦን ክፍያ በተሰብሳቢ ዓመታዊ የዓረቦን ክፍያ እንዲጣጣ ይደረጋል፡፡

፫/ በፌደራል መንግሥት ዋስትና ወይም ተሰብሳቢ የዓረቦን ክፍያዎችን ጨምሮ የራሱን ንብረቶች እና/ወይም ሌሎች ዋስትናዎችን በማስያዝ ፈንዱ ሊበደር ይችላል::

2/ The amount of annual premium paid in advance under Sub-Article (1) paragraph (c) of this Article shall be adjusted against future annual premiums.

3/ Loans drawn by the Fund may be secured by a guarantee issued by the Federal Government, or by Fund's assets, including Fund's future claims on members for premium contributions.

፲፱. የፈንዱ ሀብት አጠቃቀም

19. Use of the Fund's Resources

የፈንዱ ሀብት፡-

The Fund´s resources may be used for:

፩/ የፈንዱን ካፒታልና መደበኛ ወጪዎች ለመሸፈን፣

1/ capital expenditure and recurrent expenses of the Fund;

፪/ በመድን የተሸፈኑትን ተቀማጭ ገንዘቦች ለወደቁ የፋይናንስ ተቋማት አስቀማጮች ተመላሽ ለማድረግ፣

2/ refund of insured deposits to depositors of failed financial institutions;

፫/ በመንግሥት ሠነዶች ወይም በመንግስት ዋስትና ሠነዶች ፣ ወይም በፈንዱ በፀደቀ ማንኛውም ሌላ መስክ፣ ኢንቨስት ለማድረግ፣

3/ investment in government securities issued or securities guaranteed by the government; or any other investment mode as approved by the Fund; or

፬/ በመድን የተሸፈኑትን ተቀማጭ ገንዘቦች ክፍያ ለ ፈጸም ፈንዱ ለወሰዳቸዉ ብድሮች ክፍያ፣ ሊዉል ይችላል፡፡

4/ Servicing of loans used by the Fund for paying insured deposits.

፳. የሂሣብ ዓመት፤ የሂሣብ መግለጫዎች እና አዲት

20. Financial Year, Financial Statements and Audits

፩/ የፈንዱ የሂሣብ ዓመት እንደ አውሮፓውያን የዘመን አቆጣጠር ሐምሌ ፩ ቀን ጀምሮ በሚቀጥለው ዓመት ሰኔ ፴ ቀን ያበቃል፡፡

1/ The financial year of the Fund shall begin on July 1 and end on June 30 of the next year.

፪/ ፈንዱ ትክክለኛ እና የተሟላ የሂሣብ መዝገቦችን ይይዛል፡፡

2/ The Fund shall keep accurate and complete books of accounts.

፫/ የፈንዱ የሂሣብ መግለጫዎችና ተያያዥ ማስታወሻዎች የሚዘጋጁት በፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ አዋጅ ቁጥር ፹፬፵፯/፪ሺ፮ መሠረት ይሆናል፡፡

3/ The financial statements and related notes to accounts shall be prepared by the Fund in accordance with Financial Reporting Proclamation No. 847/2014.

፬/ የፈንዱ የሂሣብ ዓመት ባለቀ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ፈንዱ ኦዲት ያልተደረገ የሂሣብ መግለጫ አዘጋጅቶ ለቦርድ ያቀርባል፡፡

4/ The Fund shall, within one month from the end of each financial year, prepare and submit to the Board unaudited financial statements.

https://chilot.me

፭/ ቦርዱ በየ፫ (ሦስት) ዓመቱ የውጪ ኦዲተር ይሾማል፡፡ ሆኖም ኦዲተሩ የትኛዉም ዓይነት ጉድለት ከታየበት ሊቀይረዉ ይችላል፡፡ የኦዲት ሪፖርቱ ከተጠናቀቀ በኋላ እያንዳንዱ የሂሣብ ዓመት ባለቀ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ መርምሮ እንዲያፀድቀው ለቦርዱ መቅረብ አለበት፡፡

5/ The Board shall appoint an external Auditor every 3 (three) years. However, it may change the Auditor in case of any shortcomings observed. The audit report shall be completed and issued to the Board for review and approval, within six months from the end of each financial year.

፮/ በኦዲተር በሚገባ የተመረመረ እና የተፈረመ እንዲሁም በቦርዱ የፀደቀ የሂሣብ መግለጫ ለብሔራዊ ባንክ ይላካል እንዲሁም ፈንዱ በሚያወጣው ዓመታዊ ሪፖርት ውስጥ ታትሞ ይወጣል፡፡

6/ The financial statements duly audited, approved by the Board and signed by Auditor shall be submitted to the National Bank and published in the annual report to be issued by the Fund.

ክፍል አራት

ስለመድን ክስተት፣በመድን ስለሚሸፈኑና ስለተሸፈኑ ተቀማጭ ገንዘቦች

PART FOUR

INSURANCE EVENT, INSURABLE AND INSURED DEPOSITS

፳፩. ስለመድን ክስተት

የወደቁ የፋይናንስ ተቋማት የሥራ ፈቃድ የተሰረዘ መሆኑን ብሔራዊ ባንክ በሚያውጅበት ጊዜ እና በዚህ ደንብ መሠረት ፈንዱ በመድን የተሸፈነውን የተቋሙን ተቀማጭ ገንዘብ ለመክፈል ሲወስን የመድን ክስተት ይፈጠራል፡፡

21. Insurance Event

An insurance event shall occur on the date when the National Bank announces the revocation of a business license of the failed financial institutions and the Fund undertakes to pay the insured deposits under this Regulation.

፳፪. በመድን ስለሚሸፈኑ ተቀማጭ ገንዘቦች

በመድን የሚሸፈን ተቀማጭ ገንዘብ በአባል ፋይናንስ ተቋም ከገንዘብ አስቀማጭ ወይም ከተወካዩ የተሰበሰበ ተቀማጭ ገንዘብ ሲሆን፣ የሚከተሉትን አያካትትም፡-

22. Insurable Deposits money

An insurable deposit money is a deposit received by a member financial institution from or on behalf of a depositor with the exception of the following:

፩/ የመድን ሰጪ፣ የካፒታል ዕቃ አከራይ ኩባንያ ወይም የሌላ ፋይናንስ ተቋም ተቀማጭ ገንዘብ፣

1/ deposits of an insurer, a capital goods lease company or another financial institution,

፪/ የመንግሥት ወይም የመንግሥታዊ ድርጅት ተቀማጭ ገንዘብ፣

2/ deposits money of Government or an agency of the Government;

https://chilot.me

፫/ የአባል ፋይናንስ ተቋም ተደማጭነት ያለው ባለአክሲዮን፣ ዳይሬክተር፣ ዋና ሥራ አስፈጻሚ፣ ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚ፣ እና/ወይም ከተጠቀሰው ባለአክሲዮን፣ ዳይሬክተር፣ ዋና ሥራ አስፈጻሚ፣ ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚ ጋር የትዳር ወይም የመጀመሪያ ደረጃ የሥጋ ዝምድና ያለው ሰው፣ እና የአባል ፋይናንስ ተቋም ተደማጭነት ያለው ባለአክሲዮን፣ ዳይሬክተር፣ ዋና ሥራ አስፈጻሚ፣ ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚ፣ እና/ወይም ከተጠቀሰው ባለአክሲዮን፣ ዳይሬክተር፣ ዋና/ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚ እና/ወይም ከእነዚሁ ባለአክሲዮን፣ ዳይሬክተር፣ ዋና ሥራ አስፈጻሚ፣ ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚ ጋር የትዳር ወይም የመጀመሪያ ደረጃ የሥጋ ዝምድና ያለው ሰው ከአሥር በመቶ በላይ ድምፅ የሚሰጥበት ሕጋዊ ሰዉነት ያለዉ አካል ተቀማጭ ገንዘቦች፣

3/ deposits of an influential shareholder, a director, or a chief executive officer, senior executive officer of a financial institution and/or spouse or relation in the first degree of consanguinity or affinity of such shareholder, director, chief executive officer, senior executive officer of a financial institution; and that of a legal entity in which the influential shareholder, director, chief executive officer, senior executive officer of a financial institution and/or spouse or relation in the first degree of consanguinity or affinity of such influential shareholder, director, chief executive officer, senior executive officer of a financial institution holding in excess of 10% of the voting rights;

፬/ የአባል ፋይናንስ ተቋም የውጭ ኦዲተርና የሽሪኩ ተቀማጭ ገንዘብ፣

4/ deposits of an external Auditor of the member financial institution and his partner,

፭/ የተቀማጭ ገንዘብ ሂሳብና የብድር ሂሳብ ያለው ሰዉ ሲኖርና ተቀማጩ ገንዘብ ለዕዳዉ በዋስትናነት የተያዘ ከሆነ፣

5/ counterclaims from a person who maintains both deposit and loan accounts, the former serving as a collateral for the loan;

፮/ በፍርድ ቤት ውሳኔ የታገዱ ተቀማጭ ገንዘቦች፣ እና

6/ deposits frozen by the court decission ;

፯/ በየጊዜዉ በፈንዱ የሚወሰኑ ሌሎች ተቀማጭ ገንዘቦች፡፡

7/ Such other deposits as may be specified from time to time by the Fund.

፳፫. <u>በመድን ስለሚሸፈን ተቀማጭ ገንዘብ መጠን</u>

23. <u>Amount of the Insurable Deposits</u>

፩/ በመድን የሚሸፈን ተቀማጭ ገንዘብ መጠን በእያንዳንዱ የፋይናንስ ተቋም የሚወሰነው አስቀማጩ በፋይናንስ ተቋሙ የተለያዩ ሂሳቦች ዉስጥ ያስቀመጣቸዉንና በመድን የሚሸፈኑትን የተቀማጭ ገንዘቦች በሙሉ በመደመር ይሆናል፤ ይህም የመድን ክስተት እስከተፈጠረበት ዕለት ድረስ በተቀማጭ ገንዘቡ ላይ የተጠራቀመውን ወለድ የሚጨምር ይሆናል፡፡

1/ The total amount of the insurable deposits of a depositor shall be determined by a financial institution by adding up all the insurable deposits of that depositor maintained in the different accounts, including the accrued interest on those deposits up to the date of the occurrence of the insurance event.

፪/ ተቀማጭ ገንዘቦቹ የተቀመጡት በዉጭ ምንዛሪ ከሆነ የፋይናንስ ተቋሙ የመድን ክስተት በተፈጠረበት ዕለት የሚኖረውን የመግዣ የምንዛሪ ተመን በመጠቀም ወደ ብር ይቀይራቸዋል፡፡

2/ In case where the deposits are denominated in foreign currency, the financial institution shall establish the equivalent amount in Birr at the buying exchange rate on the date of occurrence of the insurance event.

https://chilot.me

፫/ የመድን ክስተት በተፈጠረበት ዕለት አስቀማጩ ለፋይናንስ ተቋሙ የሚፈፅማቸዉ ክፍያዎች ወይም የሚወጣቸዉ ግዴታዎች ካሉ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፳፪/፩ ላይ ከተጠቀሰው የመድን ክፍያ ተቀናሽ ይደረጋል፡፡

3/ When a depositor has obligations towards the financial institution, which are due on the date of occurrence of the insurance event, the amount referred to in Article 22(1) of this regulation here in above shall be reduced by such amount.

፬/ አስቀማጮቹ ከዚህ የተለየ ማስረጃ ካላቀረቡ በስተቀር በጋራ የተቀመጠ ገንዘብ በአስቀማጮቹ እኩል እንደተዋጣ ይቆጠራል፡፡

4/ In case of a joint deposit, the contributions of each depositor in the common account shall be considered equal, unless those depositors submit evidence to the contrary.

፭/ የተቀማጭ ዉል የተፈረመዉ ለሦስተኛ ወገን ጥቅም (የአደራ ሂሳብ) ከሆነ በውሉ ካልተጠቀሰ በቀር ገንዘቡ የተቀመጠለት ሰው የተቀማጭ ገንዘብ መድን ካሳዉ ተከፋይ ይሆናል፡፡

5/ In case of a deposit contract for the benefit of a third party (trust account), the person on whose behalf the deposit was placed shall be entitled to claim payment from the Fund, unless otherwise stipulated in the contract.

፮/ በአባል የፋይናንስ ተቋም ወይም በሦስተኛ ወገን በዋስትና የተያዘ ተቀማጭ ገንዘብ ሲኖር በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት በመድን በሚሸፈነዉ ጠቅላላ ተቀማጭ ገንዘብ ውስጥ ይካተታል፣ ሆኖም ተቀማጭ ገንዘቡ ከዋስትና ነጻ እስኪሆን ድረስ በመድን ከተሸፈነዉ ተቀማጭ ገንዘብ ላይ ተቀንሶ ሳይከፈል እንዲቆይ ይደረጋል፡፡

6/ The deposit that serves as collateral for the member financial institution or a third party shall be included in the total amount as per Sub Article (1) of this Article , however part of the insured deposit payable for such a deposit shall be withheld until the deposit is freed from collateral.

፯/ በመድን ከሚሸፈነዉ የተቀማጭ ገንዘብ ዉስጥ እስከ ተቀማጭ ገንዘብ መድን ሽፋን ጣሪያ ድረስ ያለዉ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት በመድን የተሸፈነ ተቀማጭ ይሆናል፡፡ ፈንዱም በእያንዳንዱ አባል የፋይናንስ ተቋም በመድን የተሸፈኑትን ተቀማጭ ገንዘቦች ለእያንዳንዱ አስቀማጭ ይከፍላል፡፡

7/ Insurable deposits as per Sub Article (1) of this Article here in above up to the coverage limit of the Fund shall be insured deposits. The Fund shall pay insured deposits per a depositor per a member financial institution.

፰/ የፈንዱ የተቀማጭ ገንዘብ መድን ሽፋን ጣሪያ በቦርዱ ይወሰናል፤ ሆኖም ጣሪያዉ ከብር ፩፻ሺ (አንድ መቶ ሺህ ብር) ማነስ የለበትም፡፡

8/ The coverage limit of the Fund shall be set by the Board, however, may not be less than Birr 100,000 (One Hundred Thousand Birr).

https://chilot.me

ክፍል አምስት

አባልነትና በመድን የተሸፈነ የተቀማጭ ገንዘብ ክፍያ

፳፬. የፈንዱ አባልነት

፩/ የትኛዉም የፋይናንስ ተቋም በዚህ ደንብ ድንጋጌዎች መሠረት የፈንዱ አባል ይሆናል፡፡

፪/ ይህ ደንብ ከወጣ በኋላ የሚመሠረት የፋይናንስ ተቋም የፈንዱ አባልነት ተቋሙ የሥራ ፈቃድ ካገኘበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፪/ መሠረት የፈንዱ አባል የሚሆን የፋይናንስ ተቋም በፈንዱ የሚወሰነውን መነሻ የዓረቦን ክፍያ ይፈጽማል፡፡

፬/ የአባል ፋይናንስ ተቋማት መብቶችና ግዴታዎች ፈንዱ ከተቋማቱ ጋር በሚገባዉ የአባልነት ውል ውስጥ በዝርዝር ይገለፃል፡፡

፳፭. ከአባልነት ስለመሰናበት

፩ / ማንኛዉም አባል የፋይናንስ ተቋም፡-

ሀ) የተሰጠዉ የሥራ ፈቃድ በብሔራዊ ባንክ ተመላሽ ከተደረገ፣ ከተሰረዘ፣ ወይም ከተነጠቀ፤

ለ) በፋይናንስ ተቋሙ ላይ የመፍረስ ውሳኔ ከተላለፈበት፤

ሐ) የአባል የፋይናንስ ተቋም ተቀማጭ ገንዘቦች ሙሉ በሙሉ ወደ ሌላ የፋይናንስ ተቋም ከተላለፉ፤

መ) በአባል የፋይናንስ ተቋም በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የመፍረስ ጥያቄ መሠረት የንብረት አጣሪ ከተሾመ፤

ሠ) አባል የፋይናንስ ተቋም ከሌላ የፋይናንስ ተቋም ጋር ሲቀላቀል ወይም ሲዋሃድ፤ ወይም

PART FIVE

MEMBERSHIP AND PAYMENT OF INSURED DEPOSITS

24. Membership of the Fund

1/ Any financial institution shall be a member of the Fund according to the conditions laid down in this Regulation.

2/ Membership of a financial institution that is established after the effective date of this Regulation shall start on the date of issuance of the business license.

3/ The financial institution becoming a member of the Fund under Sub-article (2) of this Article shall pay a fixed initial premium to be determined by the Fund.

4/ Rights and obligations of the member financial institutions shall be laid down in a membership contract to be signed between the Fund and the member financial institutions.

25. Cessation of Membership

1/ A financial institution shall automatically cease being a member of the Fund upon:

a) surrender, cancellation or revocation of a member financial institution license by the National Bank;

b) issuance of a winding-up order against the member financial institution;

c) transfer of all deposit liabilities of a member financial institution to any other financial institution;

d) appointment of a liquidator in pursuance of a resolution for the member financial institution voluntary winding up;

e) merger or amalgamation of the member financial institution with any other financial institution; or

https://chilot.me

ረ) በፈንዱ ተቀባይነት ያለው ሌላ ተመሳሳይ ሁኔታ ሲከሰት፤

ከፈንዱ አባልነት ወዲያው ይሰናበታል፡፡

፪/ የአባል የፋይናንስ ተቋሙ አባልነት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት እንደተቋረጠ ፈንዱ በተቻለ ፍጥነት የተቋሙን ስም በአገሪቱ በስፋት በሚሰራጩ ቢያንስ በሁለት ዕለታዊ ጋዜጦች ታትሞ እንዲወጣ ያደርጋል፡፡

f) Happening of any other similar factor acceptable to the Fund.

2/ The Fund shall, as soon as reasonably practica ble after termination of membership of a member financial institution under Sub-Article (1) of this Article, cause the name of that member financial institution to be published in at least two daily newspapers of nationwide circulation.

፳፮. ከአባልነት መሰናበት ስለሚያስከትለው ዉጤት

በዚህ ደንብ አንቀጽ /፳፭/ በተጠቀሰው መሠረት የፈንዱ አባል የፋይናንስ ተቋም ከአባልነት ሲሰናበት የፋይናንስ ተቋሙ፡-

፩/ ከአባልነት ከመሰናበቱ በፊት ለፈንዱ ከነበሩበት ግዴታዎች ወይም ዕዳዎች ነፃ አይሆንም፡፡

፪/ ለሌላ የፋይናንስ ተቋም ሊተላለፍ ወይም ሊሰጥ ይችል በነበረ ተቀማጭ ገንዘብ ላይ ፈንዱ ለገንዘብ አስቀማጮች የፈፀመዉን ክፍያ ተመላሽ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

26. Effect of Cessation of Membership

Where a member financial institution ceases to be a member of the Fund as specified in Article 25 of this regulation , the financial institution shall:

1/ not be relieved from its obligations or liabilities to the Fund that have accrued before the cessation of its membership; and

2/ indemnify the Fund in the event of any payment made by the Fund to depositors, in respect of such deposits as shall have been transferred or acquired by another financial institution.

፳፯. በመድን ስለተሸፈነ ተቀማጭ ገንዘብ ክፍያ

፩/ የመድን ክስተት ከተፈጠረ ፈንዱ የአባል ፋይናንስ ተቋሙን ዕዳዎች በመድን እስከተሸፈነዉ ተቀማጭ ድረስ ለገንዘብ አስቀማጮች ክፍያ ይፈጽማል፡፡

፪/ በፈንዱ እምነት ከወደቀ የፋይናንስ ተቋሙ ያተረፈ የገንዘብ አስቀማጭ በመድን የተሸፈነ ተቀማጭ ገንዘብ ክፍያ አያገኝም፡፡

፫/ ፈንዱ በመድን የተሸፈነዉን ተቀማጭ ገንዘብ ክፍያ ቦርዱ በሚወስነዉ የፋይናንስ ተቋም በኩል ይፈጽማል፡፡

27. Payment of Insured Deposits money

1/ In case of the insurance event, the Fund shall pay the member financial institution´s liabilities to its depositors up to the amount of the insured deposits.

2/ A depositor, who the Fund believes profited from the failed financial institution, shall not be entitled to the payment of the insured deposits.

3/ The Fund shall repay the insured deposits through a financial institution determined by the Board.

https://chilot.me

፬/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፴፬ በባንክ ሥራ አዋጅ ቁጥር ፭፻፺፪/፪ሺ (እንደተሻሻለ) አንቀጽ /፴፫/ እና በአነስተኛ የፋይናንስ ሥራ አዋጅ ቁጥር ፮፻፳፮/፪ሺ፩ (እንደተሻሻለ) አንቀጽ /፲፱/ መሠረት ለአባል ፋይናንስ ተቋሙ የተሾመ ሞግዚት ሹመቱ በተሰጠው በ፲፬ (አሥራ አራት) ቀናት ውስጥ በመድን ስለሚሸፈኑ የአባል ተቋሙ ተቀማጭ ገንዘቦች የጽሑፍ መዛግብትንና ደጋፊ ሰነዶችን ለቦርዱ ማቅረብ አለበት፡፡

4/ The appointed receiver of the member financial institution, as per Article 34 of this Regulation and Article 33 of the Banking Business Proclamation No. 592/2008 (as amended) and Article 19 of Micro-Financing Business Proclamation No. 626/2009 (as amended), shall submit to the Board written records and supporting documentation on the insurable deposits of that member financial institution within fourteen (14) days from the date of such appointment.

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፬/ የተጠቀሱትን የጽሑፍ መዛግብትና ደጋፊ ሰነዶች በተቀበለ በ፲፬ (አስራ አራት) ቀናት ውስጥ ፈንዱ ለገንዘብ አስቀማጮች ክፍያ የሚጀምርበትን ቀን፣ ቦታና በመድን የተሸፈኑትን ተቀማጭ ገንዘቦች ክፍያ ለመፈጸም የሚያስፈልጉትን ሰነዶች በተመለከተ ቢያንስ በሰፊዉ በሚሰራጭ አንድ ጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣ ያደርጋል፡፡

5/ Within fourteen (14) days from receipt of the records and documents mentioned under Sub-Article (4) of this Article, the Fund shall publish information in at least a widely circulating newspaper the date when repayment to depositors will start, the place where payments will be effected and the documents required for effecting payment of insured deposits.

፮/ ለገንዘብ አስቀማጮች የሚፈጸመዉ ክፍያ የመድን ክስተቱ በተፈጠረ ከ፺ (ዘጠና) ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ዉስጥ መጠናቀቅ ይኖርበታል፡፡

6/ Repayment of depositors shall end no later than 90 (ninety) days from the day of occurrence of the insurance event.

፯/ በበቂ ምክንያቶች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፮/ በተጠቀሰዉ ጊዜ ዉስጥ ቀርበዉ ክፍያ ያልተፈጸመላቸው የገንዘብ አስቀማጮች በመድን የተሸፈኑትን ተቀማጭ ገንዘቦች ክፍያ የተጠቀሰዉ ጊዜ ካለፈ በኋላም ቢሆን መጠየቅ ይችላሉ፡፡ ሆኖም የመድን ክስተቱ ከተፈጠረ ከ፭ (አምስት) ዓመታት በኋላ ፈንዱ ከማናቸዉም ተዛማጅ ዕዳዎች ነጻ ይሆናል፡፡

7/ Depositors missing the deadline in Sub-Article 6 of this Article for justifiable reasons shall claim refund of their insured deposits even after the deadline. However, latest five years after the insurance event, the Fund shall be relieved of all respective liabilities.

፰/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፯/ መሠረት በቀነ-ገደቡ ዉስጥ ክፍያ ባልተፈፀመባቸዉ ተቀማጭ ገንዘቦች ላይ ፈንዱ ለገንዘብ አስቀማጮቹ ወለድ አይከፍልም፡፡

8/ The Fund shall not pay interest on insured deposits to depositors missing the deadline in line with Sub-Article 6 of this Article.

https://chilot.me

፱/ በመድን የተሸፈኑትን ተቀማጭ ገንዘቦች በመክፈል ፈንዱ እስከ ከፈለዉ የገንዘብ መጠን ድረስ ከፋይናንስ ተቋሙ አንጻር አስቀማጩን ይተካል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ፈንዱ በባንክ ሥራ አዋጅ ቁጥር ፭፻፺፪/፪ሺ (እንደተሻሻለ) አንቀጽ /፵፭/ መሠረት ከይገባኛል ጥያቄ አከፋፈል ቅደም ተከተል አኳያም አስቀማጮቹን ይተካል፡፡

9/ By effecting payment of the insured deposits, the Fund shall assume the place of the depositor versus the financial institution up to the amount paid. The Fund shall also assume the depositors' place in the priority schedule as per Article 45 of the Banking Business Proclamation No. 592/2008 (as amended).

፲/ ራሱ ሞግዚት ሆኖ ካልተሾመ ለገንዘብ አስቀማጮች ስለፈጸማቸዉ ክፍያዎች ፈንዱ ለሞግዚቱና ለብሔራዊ ባንክ በየጊዜዉ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

10/ The Fund shall regularly inform the Receiver and the National Bank on the payments it effected to the depositors in case where it is not appointed as Receiver

ምዕራፍ ስድስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

PART SIX

MISCELLANEOUS PROVISIONS

፳፰. መረጃን ስለማግኘት፣ ስለመጠቀምና ስለመለዋወጥ

28. Information Access, Use and Exchange

፩/ ፈንዱና ብሔራዊ ባንክ፡-

1/ The Fund and the National Bank shall enter into agreement in the form of Memorandu m of Understanding which shall provide the following:

ሀ) ፈንዱን በመወከል ብሔራዊ ባንክ የሚያከናዉነዉን የቁጥጥር ሥራ፣

a) the undertaking of examination by the National Bank on behalf of the Fund;

ለ) ጤነኛ ስላልሆኑ አባል የፋይናንስ ተቋማት የመረጃ ልዉዉጥን፣

b) exchange of information with respect to member financial institutions with poor financial soundness;

ሐ) መረጃ እና/ወይም ዳታ ልዉዉጥን፣ እና

c) sharing of information and/or data; and

መ) ፈንዱ አስፈላጊ የሚላቸውን ሌሎች ጉዳዮች፣

d) Any other matters considered necessary by the Fund.

በማካተት በመግባቢያ ሰነድ መልክ ዉል ይገባሉ፡፡

፪/ ለመድን ክስተት ቅድመ-ዝግጅት ከማድረግ አንፃር መረጃ ልዉዉጥን የሚያሳልጥ ሲስተምና ሶፍትዌር መጠቀም እንዲቻል ፈንዱ ከአባል የፋይናንስ ተቋማት ጋር በትብብር ይሠራል፡፡

2/ In preparation for the insurance event, the Fund shall work with member financial institutions to ensure that there are adequate systems and software for the transfer of data.

https://chilot.me

፳፱. በፋይናንስ ተቋም ላይ ስለሚካሄድ ልዩ ምርመራ

፩/ በአባል የፋይናንስ ተቋም ላይ ልዩ ምርመራ እንዲያካሂድና ግኝቱን እንዲያቀርብለት ፈንዱ በማናቸውም ጊዜ ብሔራዊ ባንክን መጠየቅ ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የተደነገገው ቢኖርም የዚህን ደንብ ዓላማዎች ለማሳካት በፈንዱ የዚህ ዓይነት ምርመራ አስፈላጊነት ሲታመንበት የአባል የፋይናንስ ተቋሙ ያለበትን ሁኔታ ለማየት ፈንዱ በማናቸውም ጊዜ በአባል የፋይናንስ ተቋሙ ላይ ልዩ ምርመራ የማካሄድ ሥልጣን አለዉ፡፡

፫/ ለዚህ አንቀጽ ተፈጻሚነት የፈንዱ ኃላፊዎች ወይም በፈንዱ የሚሾም የትኛዉም ሌላ ሰዉ ከአባል የፋይናንስ ተቋሙ አንድ ኃላፊ፣ አዲተር፣ ወኪል ወይም ሌላ ሰዉ ፈንዱ የሚፈልጋቸዉን እንደ ሰነድ፣ ህትመት፣ መረጃ ወይም ማብራሪያ ያሉትን ጠይቆ የመቀበል ሥልጣን አላቸዉ፡፡

፬/ ፈንዱ የሚያደርገዉን ልዩ ምርመራ እንዳጠናቀቀ የምርመራዉን ሪፖርት ለብሔራዊ ባንክ መላክ አለበት፡፡

፭/ ልዩ ምርመራዉን ለማካሄድ ያወጣቸዉን ወጪዎች በተሰብሳቢ ሂሳብ በመያዝ ምርመራዉ የተደረገበት የፋይናንስ ተቋም እንዲተካለት ፈንዱ ሊጠይቀዉ ይችላል፡፡

29. Special Examination of a Financial Institution

1/ The Fund may, at any time, request the National Bank to carry out a special examination of a member financial institution and to avail to the Fund the information obtained from such examination.

2/ Notwithstanding the provision of Sub-Article 1 of this Article, the Fund shall have power to conduct a special examination of any member financial institution whenever the Fund deems such examination necessary to determine the condition of such member financial institution for purposes of this Regulation.

3/ For purpose of this section, the officers of the Fund or any other person appointed by the Fund shall have powers to require an officer, auditor, agent or any other person of the member financial institution to furnish such document, material, information or explanations as the Fund may require.

4/ Upon completion of a special examination, the Fund shall send examination report to the National Bank.

5/ The Fund may recover any cost of special examinations from the financial institution examined as a debt due and payable to the Fund.

፴. መረጃ ስለመሰብሰብና ስለመስጠት

፩/ ፈንዱ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት በአግባቡ ለመወጣት የሚያስፈልገዉን ማንኛዉንም መረጃ ከብሔራዊ ባንክና ከፋይናንስ ተቋማት መቀበል ይችላል፡፡

፪/ መረጃዉ የሚሰጠዉ፦

30. Collecting and Disclosure of Information

1) The Fund shall be empowered to collect any information both from the National Bank and the member financial institutions as it may deem appropriate to carry out its duties and responsibilities.

2) The Fund shall not disclose the information it collected using its authority under Sub-Article (1) of this Article to any person, whether within or outside Ethiopia unless the disclosure is:

https://chilot.me

ሀ) በዚህ ደንብ የተጠቀሱትን ድንጋጌዎች ለማስፈጸም፣

ለ) የፋይናንስ ተቋማትን ጤናማነት ለማረጋገጥ፣

ሐ) መረጃዉን ለመቀበል ሕጋዊ ሥልጣን ላላቸዉ፣

መ) ፈንዱ ተጠሪ ለሆነለት አካል፣

ሠ) በፍርድ ቤት ሲታዘዝ፣ ወይም

ረ) ኢትዮጵያ የገባችባቸውን የዓለም አቀፍ ግዴታዎች ለመወጣት ሲባል፣

ካልሆነ በስተቀር ፈንዱ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተሰጠዉ ሥልጣን መሠረት የተቀበለዉን መረጃ ኢትዮጵያ ዉስጥም ሆነ ከኢትዮጵያ ዉጪ ላለ ማንኛዉም ሰዉ አሳልፎ አይሰጥም።

a) made for the purpose of fulfilling the requirements of this Regulation;

b) in the interest of ensuring the financial soundness of financial institutions;

c) made to recipients who are legally authorized to obtain such information;

d) made to the body to which the Fund is accountable;

e) ordered by a court; or

f) required for the purpose of meeting obligations which Ethiopia entered into under international agreements.

፴፩. <u>ፈንዱን በሞግዚትነት ስለመሾም</u>

ብሔራዊ ባንክ በባንክ ሥራ አዋጅ ቁጥር ፭፻፺፪/፪ሺ (እንደተሻሻለ) አንቀጽ /፴፫/ እንዲሁም በአነስተኛ የፋይናንስ ሥራ አዋጅ ቁጥር ፮፻፳፭/፪ሺ (እንደተሻሻለ) አንቀጽ ፲፱ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ፈንዱን የየትኛዉም ፋይናንስ ተቋም ብቸኛ ሞግዚት አድርጎ ሊሾመዉ ይችላል።

31. <u>Appointment of the Fund as Receiver</u>

The National Bank may, whenever the circumstances require, appoint the Fund to be the sole and exclusive receiver of any financial institution and in accordance with Articles 33 of Banking Business Proclamation No. 592/2008 (as amended) and Article 19 of Micro-Financing Business Proclamation No. 626/2009 (as amended).

፴፪. <u>መመሪያዎችን የማውጣት ሥልጣን</u>

ፈንዱ ይህን ደንብ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

32. <u>Power to Issue Directives</u>

The Fund shall have the power to issue Directives necessary for the implementation of this Regulation.

፴፫. <u>ከብሔራዊ ባንክ ለፈንዱ የሚደረግ ድጋፍ</u>

፩/ ፈንዱ እስኪጠናከር ድረስና በምሥረታዉ ወቅት ብሔራዊ ባንክ ንብረት በመግዛትና ሥራዉን ለማከናወን የሚያስፈልጉትን ግብዓቶች በማቅረብ ለፈንዱ ድጋፍ ሊያደርግ ይችላል።

33. <u>Assistance to the Fund from the National Bank</u>

1/ The National Bank may assist the Fund, during its establishment and initial stage of operation, in procuring materials and providing resources needed to run the Fund's business.

https://chilot.me

፪/ ሆኖም ፈንዱ የብሔራዊ ባንክን የሎጂስቲክስና ሌሎች ወጪዎች ተመላሽ ያደርጋል፡፡

2/ The Fund shall, however, reimburse to the National Bank all costs related to the Fund's logistics or otherwise.

፴፬. የሠራተኞች አስተዳደር ደንብ

34. Staff Regulations

፩/ የፈንዱ ሠራተኞችና የአመራር አባላት ፈንዱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የሚተዳደሩ ይሆናል፡፡

1/ The employees and management staff of the Fund shall be administered in accordance with directive to be issued by the Fund.

፪/ የፈንዱ ሠራተኞች የደመወዝ፣ የአበል፣ የጥቅማጥቅምና የማበረታቻ ክፍያ ማዕቀፍ የመንግሥትን የፋይናንስ ተቋማት ክፍያ ከግምት ዉስጥ በማስገባት ፈንዱ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

2/ Payment of salary, allowance, benefits and incentives package to the employees of the Fund, in conformity with that of the governm ent financial institutions, shall be determined by directive to be issued by the Fund.

፫/ የተለያዩ ጥቅማጥቅሞች

3/ Various benefits

ሀ) የፌደራል መንግሥት ለፈንዱ የሥራ አስፈፃሚ አመራር አባል የመኖሪያ ቤት ይሰጣል፤ ምርጫዉ ከሆነ ግን የሥራ አስፈፃሚ አመራር አባሉ የቤት ኪራይ አበል ያገኛል፡፡

a) The Federal Government shall provide residential house to an executive management member of the Fund; however, the executive management member shall be entitled to opt for the payment of house allowance.

ለ) ሠራተኞችን ለማቆየት ሲባል፤ ፈንዱ የተለያዩ የጥቅማጥቅም ማዕቀፎችን በጥናቶች ይለያል፣ በቦርዱ ሲፀድቁም ሥራ ላይ ያውላቸዋል፡፡

b) With the purpose of retaining its employ ees, the Fund shall undertake studies on various benefits package and implement the same upon approval by the Board.

፬/ የፈንዱ የሥራ አስፈፃሚ አመራር የሠራተኞችን ቅሬታ የሚሰማና ምክረ-ሀሳብ ለሥራ አስፈፃሚ አመራሩ የሚያቀርብ ኮሚቴ ያዋቅራል፡፡ ነገር ግን በሥራ አስፈፃሚ አመራሩ አስተዳደራዊ ውሳኔ ያልረካ ሠራተኛ ቢኖር ጉዳዩን ለመደበኛ ፍርድ ቤት ሊያቀርብ ይችላል፡፡

4/ The executive management of the Fund shall establish a grievance handling committee that conducts grievance inquiry between the Fund and its employees, and submits recommendat ion to the executive management. However, an employee aggrieved by the administrative decision of the executive management may present his case to the regular courts.

፴፭. ከዓመታዊ የዓረቦን ክፍያ ዕዳ ነፃ ስለመሆን

35. Exemption from Liability to Pay Annual Premium

በዚህ ደንብ አንቀፅ ፲፮/፩/ እና ፳፬/፫/ መሠረት አባል የፋይናንስ ተቋማት የመነሻውን የዓረቦን ክፍያ በጀት ዓመቱ ከተጀመረ ከ፬ (አራት) ወራት በኋላ ከከፈሉ በዚህ ደንብ አንቀፅ ፲፮/፭/ መሠረት የዚያዉ በጀት ዓመት ዓመታዊ የዓረቦን ክፍያ ባለዕዳ ላይሆኑ ይችላሉ፡፡

If the member financial institutions paid an initial premium as per Articles 16(1) & 24(3) of this Regulation after lapse of 4 months from the financial year may not be liable to pay annual premium as per Article 16(5) of this Regulation during the same financial year.

https://chilot.me

፴፮. የፈንዱ ሠራተኞችና ወኪሎች ከግል ተጠያቂነት ስለመጠበቃቸዉ

ይህን ደንብ ለማስፈጸም ሲባል ማንኛዉም የፈንዱ ሠራተኛ ወይም ወኪል በቅን ልቦና ለሚፈጽመዉ ማናቸዉም ድርጊት በግል በዕዳ ሊጠየቅ፣ ሊከሰስ ወይም ማናቸዉም ሌላ ጥያቄ ሊቀርብበት አይችልም፡፡

36. Protection of Employees and Agents of the Fund from Personal Liability

Any employee or agent of the Fund may not be subject to any personal liability, action or any other claim for his bona fide acts done for the purpose of carrying out this Regulation into effect.

፴፯. ለሕዝብ ግንዛቤ ስለማስጨበጥ

፩/ አባል የፋይናንስ ተቋም የፈንዱ አባል ስለመሆኑና በዚህም ሳቢያ የተቀማጭ ገንዘቡ ጥበቃ እንደሚደረግለት በራሪ ወረቀቶችን ጭም ር በመጠቀም ለሕዝቡ ግንዛቤ ያስጨብጣል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ ድንጋጌ ቢኖርም የፋይናንስ ተቋሙ የፈንዱን አባልነት ራሱን ለማስተዋወቅ ዓላማ አይጠቀምበትም፡፡

37. Public Awareness

1/ A member financial institution shall inform the public about its membership in the Fund and the related protection of deposits and use the information materials provided by the Fund for this purpose.

2/ Notwithstanding the provision of Sub-Article (1) of this Article, the finanacial institution shall not use its membership for own promotional purposes.

፴፰. ቅሬታ ስለመስማት

ፈንዱ በራሱና በፋይናንስ ተቋማት መካከል የሚነሳ ዉን ማንኛዉንም ቅሬታ የሚፈታ ሥርዓት ሊዘረጋ ይችላል፡፡

38. Greviance hearing

The Fund may establish a system to resolve any dispute that may arise between the Fund and member financial institutions.

፴፱. ወቅታዊ ሪፖርቶችን ለፈንዱ ስለማቅረብ

ፈንዱ በሚጠይቀዉ አኳኋን ሁሉም አባል የፋይናንስ ተቋማት ወቅታዊ ሪፖርቶችን ለፈንዱ ያቀርባሉ ፡፡

39. Periodic Reports to the Fund

All member financial institutions shall submit to the Fund periodic reports as prescribed by the Fund.

፵. መረጃን ለሕዝብ ይፋ ስለማድረግ

፩/ ፈንዱ ቢያንስ ዋና የሥራ እንቅስቃሴውን አስመ ልክቶ በዝርዝር መረጃ በተደገፈ መልኩ ዓመታዊ ሪፖርት እያዘጋጀ ለሕዝብ ይፋ ያደርጋል፡፡

፪/ ፈንዱ ከአባል የፋይናንስ ተቋማት ጋር ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ ስብሰባ ያካሂዳል፡፡

40. Disclosure of information to the publice

1/ The Fund shall prepare and make available to the public an annual report that shall at least include statistical data of its main operation.

2/ The Fund shall conduct at least once in a year a meeting with the member financial institutions.

https://chilot.me

፵፩. ቅጣት

የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች የተላለፈ ማንኛውም ሰዉ ፈንዱ በሚያወጣዉ ዝርዝር መመሪያ መሠረት እስከ ብር ፲ሺ (አሥር ሺ ብር) እና ጥሰቱ ለተከሰተበት ለእያንዳንዱ ቀን እስከ ብር ፩ሺ (አንድ ሺ ብር) ይቀጣል።

41. Penalty

Any person who contravenes the provisions of this Regulation shall be punished with a fine not exceeding Birr 10,000 (Ten Thousand Birr) and shall be subjected to a daily penalty not exceeding Birr 1,000 (One Thousand Birr) for every day the contravention continues based on the detail directive to be prescribed by the Fund.

፵፪. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች

ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ እና ልማዳዊ አሠራር በዚህ ደንብ በተደነገጉ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም።

42. Inapplicable Law

No regulation, directive or practice may, in so far as it is inconsistent with the provisions of this Regulation, be applicable with respect to matters provided for by this Regulation.

፵፫. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

43. Effective Date

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

አዲስ አበባ የካቲት ፱ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም

Done at Addis Ababa, on this 25th day of feburary, 2020.

አብይ አህመድ (ዶ/ር)
የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ሚኒስትር

ABIY AHMED (DR.)
PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

https://chilot.me